# ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ

## ዓለም አቀፍ አመራር

## KINIJIT FOR UNITY AND DEMOCRACY PARTY
## INTERNATIONAL LEADERSHIP


# ዓለም አቀፍ የቅንጅት አመራር ስለመመስረት በቃሊቲ እስር ቤት ውስጥ ከሚገኙት የቅንጅቱ መሪዎች የተላለፈ መልእክት

የቅንጅቱ ከፍተኛ አመራሮች በኖቬምበር፣ 2005 ቢታሰሩም፤ ከዚያም ጋር ተያይዞ በመላው አገሪቱ ኢህአዴግ የጅምላ እስራት ቢፈጽምም፤ የኢትዮጵያ ህዝቦች ለነፃነት እና የራሳቸውን መንግስት ለመመስረት የሚያደርጉት ትግል ቀጥሏል። ሆኖም አሁን የጎደለውን የአመራር ክፍተት ካልሞላነው፤ ይህ ትግል ህይወት ሊያጣ ይችላል።

እኛ በእስር ላይ የምንገኝ የቅንጅቱ መሪዎች እርስ በርስ ከተመካከርን በኋላ፤ ዓለም አቀፍ ኮሚቴ በመመስረት የአመራሩን ስፍራ እንዲረከብ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን አምኖበታል።

ይህ የተሰየመው ኮሚቴም የበላይ አካል እንዲሆን ወስነናል። ሃላፊነቱም አቅጣጫ ማስያዝና የቅንጅት አካሎችን፣ አህጉራዊ ቅርንጫፎች እና የድጋፍ ሰጪዎችን መምራት ይሆናል።

በመሆኑም ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ስድስት ሰዎች፤ ቅንጅትን በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲመሩ ተወስኗል።

1- ሻለቃ ዮሴፍ ያዘው
2- አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ
3- ዶክተር ሞገስ ገብረማርያም
4- አቶ ብርሃነ መዋ
5- አቶ ዳንኤል አሰፋ
6- ዶክተር ገብረየ ወልደሩፋኤል ናቸው።

ከዚህ በተጨማሪ፣ ይህ አዲስ አመራር ሶስት ተጨማሪ ሰዎችን በመምረጥ እና በኮሚቴው ላይ በማከል ስራውን ይቀጥላል።

ይህ መመሪያ ለሁሉም የቅንጅት ቅርንጫፍ አካላትና ድጋፍ ሰጪዎች እንዲተላለፍ አዘናል። ዓለም አቀፉ አመራር የተሰጠውን ከፍተኛ የሆነ ሃላፊነት በብቃት እንዲወጣ የሁሉንም ኢትዮጵያዊያን፣ ቅርንጫፎችና ድጋፍ ሰጪዎች እንዲተባበሯቸው እና የኮሚቴውንም ውሳኔ እንዲቀበሉ እንጠይቃለን።

## ቅንጅት ያነገበው የነፃነት መንፈስ ያሸንፋል።

- ኢንጂነር ሃይሉ ሻወል
- ወ/ት ብርቱካን ሚዴቅሳ
- አቶ ሙሉነህ ኢዩኤል
- ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
ግንቦት 1998 ዓ.ም